አፍሪካ ቲቪ

3

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት ኢስላማዊ ቤተሰብ ህግጋት

በቴሌግራም 6

AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

- **ከሴቶች ጉዳዮች...**

አንድ ወንድ ዘመዱ ካልሆነች ሴት ጋር ብቻውን መሆን ወይም መቀመጥ ሐራም (ክልክል) ነው፡፡

ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ዘመዷ አብሯት ከሌለ ሴት ጋር ለብቻው አይሁን›› ብለዋል፡፡

ከሷ ጋር አባቷ፤ አያቷ፤ የአባቷ አያት፤ ወንድ ልጇ፤ የልጅ ልጇ፤ ወንድሟ፤ የወንድሞቿ ልጆች፤ የእህቶቿ ልጆች፤ አጎቷ፤ የእናቷ ወንድም አጎቷ፤ የባሏዋ አባት፤ የባሏዋ ልጅ፤ በጥቢ የሚገናኙት ወንድሟ፤ የሴት ልጇ ባል፤ የእናት ባል፡፡ ከነዚህ ውጪ ያሉት ማንኛውም ሰው ዘመድ ያልሆነ ሩቅ (አጅነቢይ) ይባላሉ፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

ሴት ልጅ ወደ መስጂድ ሂዳ መስገድ ትችላለች፡፡ ፊትና ከፈራች ግን ይጠላባታል፡፡ እናታችን አኢሻ ነብዩ ‹‹ሴቶች አሁን ያመጡትን ቢያውቁ ኑሮ የበኒ ኢስራኤል ሴቶች እንደተከለከሉ ሁሉ ይከለክሏቸው ነበር) ብለዋል፡፡ የወንድ ልጅ ሶላት በመስጊድ ሲሰገድ እጥፍ ድርብ እንደሚሆን ሁሉ የሴት ልጅ ሶላት ደግሞ በቤት ሲሰገድ እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹አንዲት ሴት ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥታ ከእርሰዎ ጋር መስገድ ደስ ይለኛል ስትላቸው አዎ! ከእኔ ጋር መስገድ ደስ እንደሚልሽ እንደምትወጂ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን በጓዳሽ ውስጥ መስገድሽ ምንዳው በቤትሽ ውስጥ ከመስገድሽ ይበልጣል፡፡ በቤትሽ ውስጥ መስገድሽ ምንዳው በግቢሽ ውስጥ ከመስገድሽ ይበልጣል፡፡ በግቢሽ መስግድሽ በሰፈርሽ መስጂድ ውስጥ ከመስገድሽ ይበልጣል፡፡ በሰፈርሽ መስጂድ ውስጥ መስገድሽ ምንዳው በእኔ መስጂድ ውስጥ ከመስገድሽ ይበልጣል፡፡) ብለዋል እንዲሁም
ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ከሴቶች መስጂዶች
የሚበልጠው ቤቶቻቸው ናቸው›› ብለዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

ሴት ልጅ አብሯት የሚሄድ ወንድ ዘመድ ካላገኘች በስተቀር ሐጅም ሆነ ዑምራ ማድረግ ግዴታ የላባትም፡፡ ያለ መህረም (ዘመድ) መጓዝም አይፈቀድላትምና ነው፡፡

ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ‹‹ሴት ልጅ ከሶስት ሌሊት በላይ የሆነን መንገድ ያለ ዘመድ እንዳትጓዝ›› ብለዋል፡፡

አፍሪካ አካዳሚ

- **ሴት ልጅ መቃብር መጎብኘት ክልክል ስለመሆኑ**

ሴት ልጅ መቃብር መጎብኘትና አስክሬን (ጀናዛ) መሸኘት ክልክል ነው፡፡

ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ‹‹ቀብር ጎብኚ ሴቶችን አላህ እርግማኑን ያውርድባቸው›› ብለዋል፡፡ ሙስሊም በዘገቡት ዘገባ ኡሙ ዐጢያ ‹‹ጀናዛ መከተል ተከልክለናል ግዴታ ግን አልተደረገብንም ነበር›› ብለዋል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

- እጮኛን በማያታልል መልኩ ሴት ልጅ ፀጉሯን ከጥቁር ቀለም በስተቀር በፈለገቻው ቀለም (ከለር) ማቅለም ትችላለች፡፡ ጥቁር ግን ይጠላል፡፡
- ሴት ልጅ አላህ የወሰነላት የውርስ ድርሻ ልትወስድ ይገባታል፡፡ መከልከሉ አይፈቀድም፡፡
- ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ) ኢብኑ ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹የወራሹን ውርስ የቆረጠ ሰው በጀነት የሚወርሰው የቂያማ እለት አላህ ይቆርጥበታል፡፡›› ብለዋል፡፡

3

አፍሪካ አካዳሚ

- ባል ሚስትን መቀለብ ግዴታው ነው። ይህም ሲባል ሴት ልጅ የሚያስፈልጋትን ልብስ ምግብ መጠለያ ያጠቃልላል። አላህ ሱ.ወ፦ «የሐብት (የችሎታ) ባለቤት በችሎታው ልክ ይቀልብ። በእርሱም ላይ ሲሳዩ የተጣበበበት ሰው አላህ ከሰጠው ይስጥ። ነፍስን የሰጣትን ያህል እንጂ አያስገድድም» ብሏል ሴት ልጅ ባል የሌላት ከሆነች አባቷ ላይ ወይም ወንድሟ ወይም ልጇ ላይ እሷን መቀለብ ግዴታ ነው። የቅርብ ዘመድ የሌላት ሴት ከሆነች የምትኖርበት ማህበረሰብ ሊቀልባት ይገባል።
- ምክንያቱም ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (ለድሆች ባል አልባዎች የሚለፋ ሰው ጂሃድ እንደወጣ ወይም ሌሊቱን ቆሞ ቀኑን ፆሞ እንደሚያሳልፍ ነው) ብለዋል።
- ሴት ልጅ እስካላገባች ድረስ ከቀድሞ ባሏ የወለደቻቸው ልጆችን በማሳደግ ላይ ሞግዚት መሆን ባለ ሙሉ መብት ናት። አባትም በዚህ ጊዜ የልጁን ቀለብ ለእናት መስጠት አለበት።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

- ሴት በተለይ ወጣት ሴት ወንዶችን በሰላምታ እንድትጀምር አይወደድላትም፡፡ ነገር ግን ከጠየቀች መመለስ ዋጂብ ነው፡፡

- በየ ጊዜው እንደ ሁኔታው ጉያን መላጨት፤ የብብትን ፀጉር መንጨት፤ ጥፈሮችን መቁረጥ ይወደዳል፡፡ እነዚህን ነገሮች ከአርባ ቀን በላይ ማዘግየት ይጠላል፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com